# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ.ም.

## የሕዝብን ትግል ለማፈን የባዕዳንን ጣልቃ ገብነት እናውግዝ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረኛው የመለስ አገዛዝ ላይ በቁጣ መነሳቱን ለማደናቀፍ ከዚህ በፊትም የሕዝብን ትግል በማጥቃት ለወያኔ የታደጉት ባዕዳን በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ትግል አጋጅ እንቅስቃሴ ጀምረዋል ፡፡ ኢሕአፓ ይህን አፍራሽ ጣልቃ ገብነት በጥብቅ እያወገዘ ታጋይ ኃይሎችና ሕዝብ ለዚህ ሴራ ሰለባ እንዳይሆኑ ያሳስባል፡፡

በረጅም የትግል ታሪኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎጂ የባዕዳንን ጣልቃ ገብነትን ታዝቧል፡፡ የሙሶሊኒ ወረራ ጊዜ የታየውን ብንተው እንኳን የ1953ቱን መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፉ የአሜሪካ ኤምባሲና ሰላዮቹ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ በ1997 የመለስ አገዛዝ በመርጫ ሽንፈተን ተከናንቦ ግን ስልጣን አለቅም በማለት ወንጀል ሲፈፅም ይህን በመቃወም የተጠራውን የሙት ከተማ አድማ ያከሸፉት አሜሪካና እንግሊዝ ሀሞተ ቢስ የሆኑ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን ይዘው መሆኑም የሚረሳ አይደለም፡፡ አሜሪካና ምዕራባውያን በወያኔ አገዛዝ ላይ ትግል እንዳይነሳ መለስ ዜናዊን በመደገፍ በጎረቤት ሀገሮችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲፈፅሙት የነበረውንና ያለውን ሻጥር ደግሞ ሕዝብ ያውቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የመለስ አገዛዝ በአፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ እየተካሄደ ያለው የሕዝብ ተቃውሞና አብዮት መጣብኝ ብሎ እየሰጋ ያለበት ወቅት ነውና ያሰጋዋልና የባዕድጡት አባቶቹን አድኑኝ ብሎ መማፀኑ ምስጢር አይደለም፡፡ በዚህም መሰረት የአሜሪካ ኤምባሲ አዛኝ ቅቤ አንጓች ሚናውን በድፍረት በመቀጠል ተቃዋሚ ነን የሚሉትን ቡድኖች በአዲሰ አበባ ማነጋገር ጀምሯል፡፡ የሕዝብን ትግል ለማፈን ከእኛም ከመለስ አገዛዝም ጋር በሕዝብ ላይ ተባበሩ የሚል ጥሪ መሆኑም ተደምጧል፡፡ አሜሪካ እያነጋገራቸው ያሉት የይስሙላ ተቃዋሚዎች ግን በሀቁ ተለጣፊዎች ቢሆኑም የባዕዳኑ ሴራ መጪውን የሕዝብ ትግል ሊያፍነው የሚችል አይደለም፡፡ሕዝብም ያምፃል፤ የወያኔም አገዛዝ ይወገዳል፡፡

የባዕዳኑን ሴራ እናክሽፍ!!
በወያኔ አገዛዝ ላይ ሕዝባዊ አመፅ ይፈንዳ!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France